

# «ቃሌ»

(ለብርቱካን ሚደቅሣ)



*ከዘፍጥረተ-ዓለም ቀዳማይ ከሁሉ፣
የእግዚአብሔር ማደሪያ ነበረ እኮ ቃሉ፤
«ቃልም ሥጋ ሆነ..»
ጸጋንና እውነታን በመንፈስ ተሞልቶ..
በእኛ ላይ ገነነ::*1

ቃል- የእምነት ምስረታ፣
ቃል- የልብ እውነታ፣
ቃል- ልዑል፣ ቃል- ክቡር፣
ከሐቀኛ አንደበት ወጥቶ እማይሰበር::

በለስ የቀናችህ እንዳሻው ለጊዜው፣
የቂም ቋጠሮህን በልብህ አስረኸው፣
ብረቱ ያንተ ነው፤ ጉልበቱም ያንተ ነው፣
ምንም ብታደርገኝ የኔ ቃል ይኸው ነው::

ቃል ለምድር ለሰማይ
መንገድህን ሳላይ!
በሕያው ብዕሩ ባለቅኔው እንዳለው፣
«ቃል የእምነት ዕዳ ነው..»!!*2

ጌታቸው አበራ
መጋቢት ፪ ሺህ ፩ ዓ/ም
(ማርች 2009)

---

*1 ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ - (ዮሐ. ምዕ. ፩)

*2 ከሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን - (እሳት ወይ አበባ)